# የአቶ መለስ መታመምና የዳያስፖራ ፖለቲካ -!

ግርማ ካሳ
(muziky68@yahoo.com)

ሐምሌ 16 ቀን 2004 ዓ.ም (July 22, 2012)

## <u>መግቢያ</u>

ሰሞኑን፣ ኢትዮጵያውያንን በስፋት እያነጋገረ ያለ አንድ ነገር አለ። እርሱም የጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ መታመም ነዉ። ምንም እንኳን የመንግስት ባለስልጣናት አቶ መለስ፣ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ የተለያዩ መግለጫዎች ቢሰጡም፣ አቶ መለስ መሞታቸዉን ፣ ካልሞቱም ደግሞ ወደ ሥራቸው ሊያስመስላቸዉ የሚችል ጤንነት እንደሌላቸዉ የሚናገሩ ጥቂቶች አይደሉም። በዚህ ሆነ በዚያ፣ በማንም ሰዉ ላይ ክፉ መመኘት ጥሩ አይደለምና መድሃኔዓለም ባሉበት ቦታ ያስባቸው እላለሁ።

ለሃያ አመታት አገርን ያስተዳደሩ እኚህ ሰው፣ ገለል ማለታቸው፣ ምን አይነት እንድምታ ሊፈጠር እንደሚችል ለመገመት ይከብዳል። ነገር ግን በእርግጠኝነት መናገር የምንችላቸው ሁለት ነገሮች አሉ። የመጀመሪያዉ ቢያንስ ቢያንስ የአቶ መለስ ዜናዊ ሕመም ትልቅ ዉይይትን በመካከላችን እንደጫረ ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ የእርሳቸው ገለል ማለት ኢትዮጵያ ያለችበትን ችግር ይፈታል ማለት እንዳልሆነ ነዉ።

አቶ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን ባስተዳደሩበት አመታት ያከናወኑት መልካም ተግባራት ሊኖሩ እንደሚችሉ ሁሉ፣ የሰሩትም በርካታ ስህተቶችና ጥፋቶች ይኖራሉ። ደጋፊዎች እንዳሏቸው ሁሉ ተቃዋሚዎችም አሏቸዉ። የአቶ መለስን ሥራ ለታሪክ ባለሞያዎች ትቼ በአሁኑ ወቅቱ ሊነሳ ወደ ሚችለዉ አንገብጋቢ ጥያቄ እመለሳለሁ። እርሱም «ከዚህ በኋላ ምንድን ነዉ የሚሆነዉ?» የሚለዉ ጥያቄ ነዉ።

## <u>በአገር ቤት ያሉ ተቃዋሚዎች</u>

እንደምናወቀው በዚህ ወቅት፣ አለ የሚባል የተደራጀና ብቃት ያለዉ የተቃዋሚ ኃይል የለም። በአገር ቤት የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ያቀፈዉ መድረክ የተሰኘዉ ስብሰብ አለ። ይህ ስብስብ እንደነ አቶ አንዱዋለም አራጌ፣ አቶ በቀለ ገርባ ያሉ አንጋፋና ጠንካራ አመራር አባላቱ፣ በቃሊት የሚሰቃዩበት፣ በአንጻራዊነት የተሻለ የሚባል የተቃዋሚዎች ግንባር ነዉ።

የመድረክ አባላት ከአገዛዙ እየደረሰባቸዉ ያለዉን ከፍተኛ አፈናና እንግልት በመቋቋም ፣ በከባድና ፈታኝ ሁኔታ ዉስጥ የተቻላቸዉን እያደረጉ ይገኛሉ። **የገንዘብ አቅም ያለዉ፣ በዉጭ አገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ፣ ከአመታት በፊት በቅንጅት ወቅት ያደርግ እንደነበረዉ፣ ይሄ ነዉ የሚባል የገንዘብ ድጋፍ ባይሰጣቸውም፣ ከዚያዉ አገር ቤት ከሚኖረዉ ድሃ ሕዝብ እርዳታ እየተሰበሰበ፣ ሴሚናሮችና ሕዝባዊ ስብሰባዎችን እያደረጉ፣ ሕዝቡን ለማደራጀት እየሞከሩ ነዉ። ፍኖት የተሰኘን ሳምንታዊ ጋዜጣ በማተምና በማሰራጨት፣ ሕዝቡ ለትግል እንዲነሳሳ፣ ከፍርሃት እንዲላቀቅ፣ ለመብቱ እንዲታገል ቅስቀሳ እየተደረገ ነዉ።** *(በአገር ቤት ያሉ ተቃዋሚዎች ቢወስዷቸዉ ይጠቅማሉ የምላቸዉን አንዳንድ ሃሳቦች በሌላ ጽሁፍ በስፋትት ይገዤ እቅርባለሁ)*

## በዉጭ አገር ያሉ  ተቃዋሚዎች

በዉጭ አገር ከፍተኛ የገንዘብ ወጭ እያወጡ፣ በኢትዮጵያ ለዉጥ እንዲመጣ እንታገላለን የሚሉ የተለያዩ ቡድኖችን ስንመለከት ደግሞ፣ የሚያሳዝነዉ፣ የትግሉን ትኩረት ከአገር ቤት ወደ ዉጭ አገር እንዲሆን ከማድረግ ዉጭ ያመጡትም ሆነ ያስገኙት አንዳች ጠቃሚና የተጨበጠ ነገር እንደሌለ ነዉ። ሌላዉ ቢቀር፣ አገር ቤት ያሉ የተቃዋሚ ድርጅቶች ትልቅ አፈና እየተደረገባቸው ፣ መድረክን መስርተዉ፣  በጋራ እየተንቀሳቀሱ ባሉበት ወቅት፣  ዉጭ ያሉቱ አሰልቺ የእንተባበር መግለጫዎች ከማውጣት ዉጭ፣ በተግባር ተስማምተዉ፣ አንድ ሆነዉ መስራት የቻሉበት ሁኔታ የለም።

ያለፉትን ስድስት ወራቶች ብቻ እንኳን እንመልከት። «የነጻነት ባቡር መጣ» በሚል መፈክር ሥር ፣ ግንቦት ሰባት/ጥምረት/በቃ/አነግ/ኦብነግ ... በተለያዩ የአዉሮፓና የአሜሪካ አገሮች ሕዝባዊ ስብሰባዎች በማድረግ፣ የዳያስፖራ የፖለቲካዉን አየር ተቆጣጠሩት። ከዳያስፖራዉ ብዙ ገንዘብ ተሰበሰበ። ብዙ ተባለ። ነገር ግን አሁን ባለንበት ወሳኝ ወቅት፣ እንደ ፖለቲካ ኃይል ሲንቀሳቀሱ፣ ሲመሩ፣ የመፍትሄ አማራጮችጭ ሲያስቀምጡ አናይም።

የነግንቦት ሰባት የነጻነት ባቡር ሲቆም፣  በዚሁ አመት ወደ ሚያዚያ ወር መጨረሻ አካባቢ ፣ አታዋ ላይ ሌሎች፣ ዉጭ አገር ተከል የሆኑ ድርጅቶችን  አሰባስቢያለሁ የሚል አንድ ሌላ ሁለተኛ ስብስብ ተቋቋመ። ሸንጎ የሚል ስም የተሰጠዉ።

ሰሞኑን ደግሞ በቀድሞ የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ መሥራች በነበሩት በዶር ፍስሃ የሚመራ ፣ አንድ የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት ካዉንስል የሚባል ሶስተኛ ስብሰብ ተመሰረተ። ዳላስ በተደረገዉ የኢትዮጵያዉያን ስፖርት ዉድድር ወቅት ነበር ይሄ ስብሰብ በኦፌሴል ይፋ የሆነዉ።

እነዚህ ሶስት ስብስቦች፣ እንኳን ኢሕአዴግን ተክተዉ አማራጭ ሊሆኑ ፣ እራሳቸው ቁጭ ብለዉ ፣ ተስማምተዉ ፣ ተነጋገረዉ፣ ችግሮቻቸዉን መፍታት ያልቻሉ ስብሰቦች ናቸዉ። «በትንሹ ያልታመነ በትልቁ ሊሾም አይችልም» እንደሚባለዉ ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አካል የሆነዉንና  ወደ አንድ ሚሊዮን የሚቆጠረዉን ዳያስፖራ አንድ ማድረግ ያልቻሉ እነዚህ  ስብስቦች፣ እንዴት አድርገዉ ነዉ 90 ሚሊዮን ሕዝብን አንድ አድርገዉ ሊያስተዳደሩ የሚችሉት?  ይሄ አንዱ ነጥብ ነዉ።

በሁለተኛነት ሊሰመርበት የሚገባ ነገር ቢኖር፣ እነዚህ ስብስቦች በዳያስፖራ ያሉ፣ ከሕዝቡ ርቀዉ የሚገኙ ስብስቦች ናቸዉ። የኢንተርኔት አገልግሎት የሚያገኝ፣ እንደ ኢሳት ያሉ ፕሮግራሞችን ሊያዳምጥ የሚችል ሕዝብ  ከ0.5% ብቻ በሆነባት  አገር፣  ከዉጭ ሆኖ መግለጫ በማዉጣት፣ በየስብሰባዎቹ ጠረቤዛ በመደብደብ እና ለሰዓታት ቃለ መጠይቆች በማድረግ፣ በኢትዮጵያ ለዉጥ ይመጣል ብሎ ማሰባቸዉ ከማስገረምና ከማሳቅም አልፎ አሳዛኝም ነዉ። ከዉጭ ሆኖ ጠዋትና ማታ የኢሕአዴግ አመራሮችን መርገም ለሃያ አመታት ተሞክሮ ያልሰራ ነዉ።

## ለዉጭዉ የተቃዋሚ ኃይል የመፍትሄ ሃሳቦች

ታዲያ ምንድን ነዉ መደረግ ያለበት የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። አንዳንድ ይጠቅማሉ የምላቸዉን ሃሳቦች እንደሚከተለዉ በትህትና ማቅረብ እፈልጋለሁ። እነዚህን ሃሳቦች ሳቀርብ፣ የኔ ሃሳብ ከሌሎች ይበልጣል በሚል አይደለም። ነገር ግን የሚደረገዉን ዉይይት ይረዳል በሚል ነዉ።

1. በዳያስፖራ ያሉ እነዚህ ሶስት ስብሰቦች ፣ ከሌሎች በተናጥል ከሚሰሩ እንደ ሶሊዳሪቲ ንቅናቄ ካሉ ደርጅቶች ጋር በመሆን ፣ በሚስማሙባቸዉ መለስተኛ ፕሮግራሞች ዙሪያ አንድ ትልቅ የዳያስፖራ ግንባር ወይም ሕብረት በአስቸኳይ በሳምንታት በሚቆጠሩ ጊዜያት ዉስጥ መፍጠር አለባቸዉ። «ልንሰማማ ነዉ፣ መስማማት አለብን ...» የሚሉ መግለጫዎቻቸዉን መስማት አንፈልግም። በየቴሌቭዥኑና ራዲዮ እየቀረቡ አያደንቁሩን። ስብሰባ እየጠሩ አያሰልቹን። የምናወቀዉን የኢሕአዴግ ሐጢያቶች አይደጋግሙብን። ከፈረሱ በፊት ጋሪ ሆነዉ አይቅደሙ። እርስ በርሳቸዉ ይነጋገሩ፣ ይሰማሙ፣ ይቀናጁ። ከዚያ በኋላ በጋራ በየከተማዉ የደረሱበትን ትልቅ ደረጃ ለሕዝቡ ቢያሳወቁ ያምርባቸዋል። ይሄንን እስካላደረጉ ድረስ ግን የእንግሊዘኛን አባባል ልጠቀምና «They are good for nothing».

2. በዉጭ አገር ያሉ የፖለቲካ መሪዎች ትሁት ሆነዉ፤ የግል ዝናና የከበሬታ ስፍራ ከመፈለግ ተቆጥበዉ፣ የአገርን ጥቅም አስቀድመው፣ በዳያስፖራ ያሉትን ኢትዮጵያዉያንን ሁሉ የሚያስተባበር ይህን አይነት ሕብረት ቢያቋቋሙ፣ ከወዲሁ ግልጽ ሊሆን የሚገባ አንድ ትልቅ ነጥብ አለ። እርሱም ይህ አዲሱ «ሕብረት»፣ በዉጭ አገር የሚገኝ እንደመሆኑ፣ ሊጫወት የሚችለዉ ሚና አገር ቤት የሚደረገዉን ትግል የመደገፍ ሚና እንደሆነ ነዉ። ይህ ሕብረት ከዉጭ ሆኖ የአገር ቤቱን ትግል መምራት አይችልም፣ ለመመራትም መሞከር የለበትም። ለመሞከር እንቅስቃሴ ቢያደርግም እንዲቆም መደረግ አለበት።

1. አንዳንድ ድርጅቶች የሚናገሩት አንዳንድ ፈሊጦች አሉ። «ሁለ ገብ» ትግል ይሉናል። ይመስለኛል «ሁለ ገብ» ትግል ማለታቸው የሰላማዊና የጠመንጃን ትግል ያጣመረ ትግል ማለታቸዉ ነዉ። «ሁለ ገብ» የሚለዉ ቃል በራሱ ከፋፋይ ቃል ነዉ። የጠመንጃ ትግል የሚያደርግ ኃይል «ሁለ ገብ» ትግል ብሎ ቢያወራ ያምርበታል። ነገር ግን ዉጭ አገር ቁጭ ብለዉ «ሁለ ገብ» ትግል ሲሉ ያስገርመኛል። እሰከምናውቀዉ ድረስ በወሬ እንጂ በተጨባጭ የትጥቅ ትግል እያደረገ ያለ ድርጅት የለም። መቼም «ግንቦት ሰባትስ ?» እንደማትሉኝ እርገጠኛ ነኝ ። በመሆኑም ይህ የዳያስፖራ ስብስብ፣ ከባዶ የጀግንነት ወሬና ፉከራ ወጥቶ፣ የሌለን ሁለ ገብ የሚባለዉን ፈሊጥ ትቶ፣ በሰላማዊ ትግል ለመታገል የወሰነ መሆን አለበት ።

2. ይህ ሕብረት ከሻእቢያ ተጽኖ ነጻ መሆን አለበት። አለበለዚያ **ከመወለዱ እንደሞተ ነዉ የሚቆጠረዉ።** በአቶ ኢሳያስ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እየተመራ ኢትዮጵያዉያንን አሰባስባለሁ ማለት የዋህነት ነዉ። አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ኢትዮጵያን ነጻ የሚያወጡ አይደሉም። አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ከመረብ ወንዝ ሰሜን የሚኖሩ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን እያረዱ ያሉ አምባገነን ሰው ናቸዉ።

3. **ይህ ሕብረት በወያኔ ጥላቻ ላይ ሳይሆን በኢትዮጵያ ፍቅር ላይ የተመሰረተ ሕብረት መሆን አለበት።** «ፀረ-ወያኔ» የሚል አባባል የማይገባኝና የማይዋጥለኝ አባባል ነዉ። አሁን በስልጣን ላይ ያለዉ አገዛዝ አንድ ወይንም ሁለት ግለሰብ አይደለም። ብዙ ደጋፊዎች በየማእዘናቱ አሉት። አብረናቸዉ ልንሰራ፣ ከዉስጥ አገዛዙ ለዉጥ እንዲያመጣ ሊረዱ የሚችሉ፣ በሳል፣ ሞደሬት ኃይሎች ኢሕአዴግ ውስጥ ይኖራሉ።

በተለይም በአሁኑ ወቅት የአቶ መለስ መታመም (ምናልባትም መሞት) ተከትሎ ፣ በኢሕአዴግ ዉስጥ ይኖራል ተብሎ በሚጠበቀዉ የስልጣን ፍክክር፣ እነዚህ ኢሕአዴግ ዉስጥ ያሉ ጥሩ ወገኖች አይለው ቢወጡ፣ እጅግ በጣም ትልቅና ጠቃሚ ነገር ነበር የሚሆነዉ። እንደ ደቡብ አፍሪካዉ ፍሬዴሪክ ደክለርክ፣ እንደ ሩሲያዉ ሚካኤል ጎርባቾቭ ያሉ ከኢሕአዴግ ዉስጥ ቢወጡ፣ አስቡት ምን አይነት አዋንታዊ ተጽእኖ እንደሚኖረዉ። ለዚህም ነዉ በጅምላ የማዉገዝ፣ አንዱን ወዳጅ ሌላዉን ጠላት አድርጎ የማየት፣ ሌላዉን ኢትዮጵያዊ የማዋረድ ፖለቲካ፣ መቆም ያለበት ፖለቲካ ነዉ የምለዉ። ይህ የሰለጠነ ፖለቲካ አይደለም። በኢሕአዴግ ዉስጥ ጥላቻ የተሞሉ አክራሪዎችንና ዘረኞች አይለው እንዲወጡ የሚረዳ ጎጂ ፖለቲካ ነዉ። የኋላ ቀር ፖለቲካ ነዉ።

የሰለጠነ ፖለቲካ ማለት ጠላት የተባለዉን ወዳጅ ማድረግ ማለት ነዉ። የሰለጠነ ፖለቲካ ማለት ከኛ በአስተያየት የሚለዩትን መሳደብ ሳይሆን ጨዋነት በተሞላበት መልኩ፣ ለማሳመን መሞከር፣ እኛም ከተሳሳትን ለመታረምና ለመማር ፈቃደኛ መሆን ማለት ነዉ።

በመሆኑም ይህ ሕብረት፣ በሚያደርጋቸው ተግባራቱ፣ ኢሕአዴግ ዉስጥ ያሉ ጥሩ ኃይሎችን የሚያግዝ መሆን አለበት። ለምሳሌ አሁን በስልጣን ያለዉ አገዛዝ እየፈጸማቸው ያሉትን ግፎች ስሜታዊ በሆነ መንገድ ሳይሆን፣ በተጨባጭና በመረጃ በአለም ቀፍ መድረኮች እያጋለጠ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከገዢዉ ፓርቲ ጋርም ለመነጋገር ቢዘጋጅ፣ ገዢዉ ፓርቲ የሚሰራቸው ጠቃሚ የሆነ ተግባራትንም መደገፍ ቢጀመር በጣም ይረዳል። በአጭሩ በወሬ ሳይሆን በተግባር ለሰላም፣ ለእርቅ መዘጋጀት አለበት።

## <u>ማጠቃለያ</u>

በዉጭ አገር የሚኖሩ ኃይላት በአንድ ላይ ተሰባስበዉ፣ በሰላማዊ ትግል ላይ እምነታቸዉን አጠናክረዉ፣ ከሻእቢያ ጥገኝነት ነጻ ወጥተዉ፣ አገር ቤት ካሉ ወገኖች ጋር እጅና ጓንት ሆነዉ፣ ለእርቅና ለሰላም ተዘጋጅተዉ በኢሕአዴግ ካሉ ሞደሬቶች ጋር መስራት የሚችሉበት ሁኔታ ከተፈጠረ እሰየዉ።

አለበለዚያ ግን በዉጭ አገር የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ መንቃት መቻል አለበት። በዉጭ አገር ያሉትን ስብስቦች አንቅሮ በመተዉ፣ አገር ቤት ከሚታገሉ ድርጅቶች ጎን መሰለፍ አለበት። አገር ቤት ያሉ ድርጅቶችን፣ በድጋፍ ድርጅቶቻቸዉ አማካኝነት አሊያም በቀጥታ መደገፍ መጀመር አለበት።

አገር ቤት ያለዉ ሕዝብ ካልተደራጀ ፣ አገር ቤት ያለዉ ሕዝብ ካልተነቃነቀ ፣ ለዉጥ ሊመጣ አይችለም። አንዳንዶች ቶሎ ሃብታም ለመሆን ሃሺሽ የሚሸጡ፣ በዚያ ምክንያት ችግር ዉስጥ የሚገቡ አሉ። በአቋራጭ ሃብታም ለመሆን ወደ ሃሺሽ ሽያጭ አንግባ። ድርጅታዊ ሥራ ሳይሰራ፣ ሕዝብ ሳይደራጅ ፣ የገንዘብ አቅም ሳይገነባ፣ በኢሕአዴግ ዉስጥ ያሉትን ወደ እኛ ለማምጣት ሳይሞከር፣ አምባገነኖችን በወሬና በዘራፉ ፖለቲካ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ለመገርሰስ አንሞክር።

*(ከዚህ ጽሁፍ ይዘት ጋር የማይስማሙ ድህረ ገጾችና የሜዲያ ቡድኖች ሊኖሩ እንደሚችሉ አስባለሁ። ነገር ግን የተለዩ ሃሳቦችን ማስተናገድ ዲሞክራሲና የዜጎችን የመጻፍ መብት ከሚያከብሩ፣ የጋዜጠኝነት የሞያ ብቃት ካላቸው የሚድያ ሰዎች የሚጠበቅ ነዉ። በመሆኑም አስተያየቶቼን ለአንባቢያኖቻቸዉ ያቀርባሉ የሚል ተስፋ አለኝ።)*

እግዚአብሄር ያክብርልኝ !